# ከቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ
# የውጭ ግንኙነት ኃላፊ፤
# ከዶ/ር ያቆብ ኃይለማርያም የተሰጠ ማብራሪያ

ኖቬምበር 15፣ 2007

**እርማት**

በኖቬምበር 7፣ 2007 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ፤ በአንዳንድ ድረ ገጾች ላይ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ህጋዊ ሰውነት የሚጎናጸፍበትን መንገድ ለመሻት፤ አንድ ጊዜያዊ አሰባባሪ ኮሚቴ መቋቋሙ ተገልጾ፤ የእኔም ስም በኮሚቴው አባልነት ሰፍሯል።

መስከረም 14 ቀን 1997 ዓ.ም አራቱ ፓርቲዎች፤ ማለትም መኢአድ፣ ኢዴአፓ-መድህን፣ ቀስተደመና እና ኢዴሊን አዋህደን ህልውናቸውን በስምምነት ከሰረዝን በኋላ፤ ቅንጅትን መስርተን ይህንኑ ፓርቲ በምርጫ ቦርድ ለማስመዝገብ ደፋ ቀና በምንልበት ወቅት፤ አቶ ልደቱ አያሌው ፍጹም ህገ ወጥ በሆነ መንገድ፤ በምዝገባው ማመልከቻና በሌሎችም ዶክመንቶች ላይ የኢዴአፓ-መድህንን ማህተም ለማሳረፍ ፈቃደኛ ባለመሆናቸውና የአመራሩ ወህኒ መውረድ ተደምሮ ምዝገባው መቋረጡ ይታወሳል።

የቅንጅት አመራር አባላት ከወህኒ እንደወጣን፤ ቀዳሚ ተግባር ብለን የጀመርነው ቅንጅቱ ህጋዊ ሰውነት የሚያገኝበትን መንገድ መሻት ነበር። ለዚህም ተግባር፣ ላዕላይ ምክር ቤቱ ወይዘሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ፣ አቶ ብሩክ ከበደና እኔም ራሴ የምንገኝበትን አንድ ኮሚቴ ሰየመ። ኮሚቴው ቅንጅት ህጋዊ ሰውነት የሚያገኝበትን ብዙ አማራጮች ደርድሮ፤ ይህንንም ለላዕላይ ምክር ቤቱ አቅርቦ፤ መመሪያ ከተቀበለ በኋላ፤ ከአማራጮቹ አንዱ "ለቅንጅት ቀና አመለካከት ከሌላቸው ሰዎች ለማስጣል ስንል ስሙን አስመዝግበነዋል" ካሉትና ፓርላማ ከገቡት ከነአቶ ተመስገንና ከአቶ መሐመድ ጋር ስብሰባዎችና ውይይቶች ተካሂደዋል።

ይኸው በላዕላይ ምክር ቤቱ የተሰየመው ኮሚቴ፤ ከነአቶ ተመስገን ጋር ተነጋግሮ፤ የቅንጅቱ አመራር፤ ከእስር ለተፈቱት የአመራር አባላት እንዲያስረክቡ ስምምነት ላይ ተደርሷል። እነአቶ ተመስገንም ይህንኑ አቋማቸውን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን፤ ይህንኑ አቋማቸውን ለኢትዮጵያ ህዝብ በተደጋጋሚ ገልጸዋል።

እንግዲህ በርክክቡ አፈጻጸም ላይ እየተነጋገርን እያለን ነው፤ ይህ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ መቋቋሙን የሚገልጽ ደብዳቤ በተለያዩ ድረ ገጾች ላይ የተገለጸው። የቅንጅት አስተባባሪ ኮሚቴ ከወጠናቸው ተግባራት ውስጥ አንዱ፤ ቅንጅትን በምርጫ ቦርድ ማስመዝገብና ህጋዊ ሰውነት የሚጎናጸፍበትን መንገድ ለመሻት ነው። የቅንጅትንም ተልእኮ ከግብ ለማድረስ፤ የተለያዩ የድርጅቱ አካላት መንቀሳቀስ የሚያስመሰግን ቢሆንም፤ በፓርቲው ውስጠ ደንብ መሰረት፤ ስርአትና ህግን በጠበቀ መልኩ መሆን ይገባዋል።

ይህ አሁን ተቋቋመ የተባለው ጊዜያዊ ኮሚቴ ሊያከናውን ያቀደው ተግባር፤ የላዕላይ ምክር ቤቱ ባቋቋመው ኮሚቴ የሚከናወንና በዚህም ስራ ብዙ እንደተጓዘ እየታወቀ፤ ለምን ሌላ ኮሚቴ ማቋቋም እንዳስፈለገ ግልፅ አይደለም። እንዲህ አይነቱን ኮሚቴ የማቋቋም ሃላፊነትና ስልጣን ያለው፤ የላዕላይ ምክር ቤቱ ሲሆን፤ ኮሚቴውም ስለመቋቋሙ በፕሬዘዳንቱ ወይም በምክትል ፕሬዘዳንቷ ፊርማ መረጋገጥ ይኖርበታል።

ስለዚህ በበኩሌ የላዕላይ ምክር ቤቱ ያልወሰነውንና በበላይ ሃላፊዎች ያልተፈረሙበት ጊዜያዊ አስባባሪ ኮሚቴ አባል አይደለሁም፤ አባል እንድሆንም የጠየቀኝ ሰው የለም። ይህንንም ለቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች በትህትና እገልጻለሁ።

ያቆብ ኃይለማርያም
የቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የውጭ ግንኙነት ኃላፊ